የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 እና 6

1. “በመንፈስ ነዳያን የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ _____።”
   ሀ) መጽናናትን ያገኛሉና
   ለ) ምድርን ይወርሳሉና
   ሐ) መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና
   መ) የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና

2. አንቀጸ ብፁዓን የምንላቸው ስንት ናቸው?
   ሀ) ዘጠኝ ለ) አራት ሐ) ስድስት መ) አስር ሠ) ሦስት

3. “ልባቸው ንጹሕ የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ _____።”
   ሀ) ምድርን ይወርሳሉና
   ለ) እነርሱ እግዚአብሔርን ያዩታልና
   ሐ) መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና
   መ) የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና

4. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን እንድናደርግ ካስተማረን ውስጥ አይመደብም?
   ሀ) ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትኼድ ዘንድ ቢያስገድድኽ ኹለተኛውን ከርሱ ጋራ ኺድ።
   ለ) ዐይን ስለ ዐይን ጥርስም ስለ ጥርስ ክፈል።
   ሐ) ቀሚስህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጐናጸፊያኽን ደግሞ ተውለት።
   መ) ቀኝ ፊትህን ለሚመታህ ግራ ፊትህን መልስለት።

5. የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ምን ተብሎ ይታወቃል?
   ሀ) አንቀጸ ምጽዋት ለ) አንቀጸ ብፁዓን ሐ) አንቀጸ ጸሎት መ) አንቀጸ ጾም

6. "ዛሬን የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው" ሲል ምን አይነት ኃዘንን ለማለት ነው?
   ሀ) እናት አባት ሞተብኝ፣ ዘመድ ርስት ሄደብኝ ብሎ ማዘን
   ለ) የራስን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን
   ሐ) የባልንጀራን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን
   መ) የሰማዕታትን መከራ፣ የክርስቶስን ሞት እያሰቡ ማዘን
   ሠ) ሁሉም
   ረ) ከ"ሀ" በስተቀር ሁሉም

7. የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቱ ነው?
ሀ) ማቴ ምዕራፍ ፩ እና 2
ለ) ማቴ ምዕራፍ 3 እና 4
ሐ) ማቴ ምዕራፍ 5, 6 እና 7
መ) ማቴ ምዕራፍ 8,9 እና ፲0

8. ጌታችን "ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም " ብሎ የጠቀሰው ምንን ነው?
ሀ) ጣዖት ለ) ስስት ሐ)ገንዘብ መ) ምግብ

9. ስለምንበላው ስለምንጠጣው እና ስለምንለብሰው እንዳንጨነቅ ጌታችን ምሳሌ ሰጥቶ ያስተማረባቸው ፍጥረታት የትኞቹ ናቸው?
ሀ) የሜዳ አበቦች
ለ) የሰማይ አእዋፋት
ሐ) የሰናፍጭ ቅንጣት
መ)ሀ እና ለ

10. ጌታችን ስለጸሎት ባስተማረበት ቦታ ላይ "ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ " ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ) በአደባባይ ለሰው እያሳየህ ጸልይ
ለ) በስውር ወደ ቤትህ ገብተህ ጸልይ
ሐ) ሕሊናህን ሰብስበህ ጸልይ
መ)ለ እና ሐ

11. ጌታችን ስለጸሎት ባስተማረ ጊዜ እንዳናደረግ ያዘዘው የቱን ነው?
ሀ) ወደ እልፍኝ እንድንገባ
ለ) በብዛት እንድንናገር
ሐ) በስውር ላለው አባታችን በስውር እንድንጸልይ
መ) ሀ እና ሐ

12. አባታችን ሆይ ብለን እንድንጸልይ ያስተማረን ማን ነው?
ሀ) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ለ) ከሐዋርያት አንዱ

ሐ) መጥመቁ ዮሐንስ
መ) ከነብያት አንዱ

13. ጌታችን ስለጾም ባስተማረበት አንቀጽ ላይ እንድናደርገው ያዘዘን የቱን ነው?
ሀ) በአደባባይ ጾመኛ እንድንባል እራስን መጉዳት
ለ) ፊትን ማጥፋትና መጠውለግ
ሐ) ፊትን መታጠብ ራስንም መቀባት
መ) መልሱ አልተሰጠም

14. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንቀጸ ምጽዋት ከተናገራቸው ውስጥ አይመደብም?
ሀ) “ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በሰዎች ፊት አድርጉ።”
ለ) “አንተስ ምጽዋትህን በምታደግርበት ጊዜ ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ።”
ሐ) “ምጽዋትህ በስውር ይሁን”
መ) መልሱ አልተሰጠም

15. ጌታችንና መድኃኒታችን ባልንጀራን ስለመውደድ ምን አስተማረ?
ሀ) የሚረግሙንን እንድንመርቅ
ለ) ለበደሉን እና ለሚያሳድዱን አጸፋውን እንድንመልስ
ሐ) ለሚጠሉን ክፉ እንድንመኝ
መ) ወንድሞቻችንን ብቻ እጅ እንድንነሳ

16. ባልን ወይም ሚስትን ለመፍታት በቂ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
ሀ) ዝሙት ለ) ሀሜት ህመም ሐ) መካንነት መ) መልስ የለም

17. ጌታችን ስለ መሐላ ምን ብሎ አስተማረን?
ሀ) ሁልጊዜ መሐላ እንድምል
ለ) ለአስፈላጊ ጉዳዮች አንድንምል
ሐ) ከቶ እንዳንምል
መ) በራሳችን እንድንምል

18. ከሚከተሉት አንዱ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ብፁዓን ናቸው አልተባሉም?
ሀ) የሚምሩ ለ) ስለጽድቅ የሚሰደዱ
ሐ) የሚያስታርቁ መ) የሚያሳድዱ

19. ከሚከተሉት ውስጥ ህግጋተ ወንጌል ውስጥ የሚመደበው የትኛው ነው?
ሀ) አትግደል
ለ) እናት እና አባትህን አክብር
ሐ) ከቶ አትማል
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን መሠረት መባ ስናቀርብ ማድረግ ካለብን ነገሮች መካከል የሚመደበው የቱ ነው?
ሀ) መባችንን በመሠዊያው ፊት አስቀምጠን አስቀድመን ከተጣላነው ወንድማችን መታረቅ ይኖርብናል
ለ) መባችንን ካቀረብን በኋላ የበደልነውን ወንድማችንን መታረቅ እንችላለን
ሐ) ያስቀየምነውን ወንድማችንን ይቅርታ ባንጠይቅ ራሱ መባ ስላቀረብን ይቅር እንዳለን ይቆጠርልናል
መ) ሁሉም መልስ ናቸው